# <u>በአትላንታ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤ ቤተክርስቲያን</u>

# <u>አዲስ የመጡት ቄስ የአባ ማቲያስን ስም ጠርቼ ካልቀደስሁ ቅር ይለኛል ብለው</u>

# <u>አልቅሰው ምእመናንን በመገዘት በቅዳሴ መጥራት ጀመሩ</u>

ከምእመናን

የብስራተ ቅዱስ ገብርኤል ቄስ መጋቢ አዲስ ይልማ ቸርነት ሕዝበ ምእመናኑ ፊት በቀኝ እጃቸው የያዙትን መሰቀል ከፍ አድርገው በማሳየት፣ በዚህ ክርስቶስ መስቀል የምታምኑ ለመሆናችሁ ቃል ግቡልኝ፣ እኔ የምላችሁን ስሙኝ በማለት ምእመናኑን በመስቀል ኃይል በመገዘት የአባ ማቲያስን ስም ጥር 25 ቀን 2006 (02/02/14) በዚህ ቤተክርስቲያን ለመጀመሪ ጊዜ ተጠራ።

ሃይማኖት የፖለቲካ መጠቀሚያ የባለ ኃይሎች አገልግሎት ሰጭ መሳሪያ ሆኖ የክርስትና እምነታችን ችግር ውስጥ ከገባ የቆየና የከረመ አባያተ ቤተ ክርስቲያናት ፣ ገደማትና ብዙ መንፈሳዊ አባቶች መሰቃያትም ከፍቶና ጐልቶ የሚታይ ሃቅ ነው። በዚህም ምእመናት በኢየሱስዊ እምነታቸው ጸንተው በጾም ጸሎት ፈጣሪ እግዚአብሔርን እያመለኩ እንዳይኖሩ በፖለቲከውና በመንፈስዊ ስብከትም በባንዳ አገሊጋዮች ታውከንና ግራእያጋቡን እንገኛለን። በተበታተነና እውነተኛ የእምነት መንገድ ፈር መልቀቅ ጾም ጸሎታችንም እንዳይሰምር ሆኖብን የአምላክ ቸርነት ርቆብናል። የወያኔ አስተዳደር የእምነትና እምነት ሥርዓታችንን አናግቶታል አፍርሶታል።የዚህም ተከታይና ፈጻሚዎች አቋቁሟል፣ እየተመራና እየተፈጸመም ይገኛል።

በዚህ ሁኔታ በቅርቡ ወደ በብስራተ ቅዱስ ገብርኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሂዶ ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ ትምህርት አገልግሎት የመጡት መጋቢ አዲስ ይልማ ስቀድስና ሳስተምር የአባ ማቲያስን የቅዱስ ሲኖዶስ ፓትርያርከን የካህናት አለቃውን ስም መጥራትና መቀደስ፣ማወደስ አለብኝ በማለት፣ በዚህ ከተቋቋመ ከአስር ዓመት በላይ ያለው ቤተክርስቲያን በወያኔ ሥርዓት አልባ የእጩ ምልመላና ጣልቃ ገብ የፓትርያርክ አስመራጭነትና ምርጫን ይህ ቤተክርስቲያን እየተቃውመና እያወገዘ ከመሆን ጋር ሹመታቸውንም ሆነ ስማቸውን የሁለቱንም ፓትርያርክ ተብየዎች ተቀብሎ ፣ተጠርቶም አይያወቅም።

እኝህ ቄስ በሁለት ወር ቆይታቸው ጊዜ ብዙ የሚያስጨንቅና የሚያሳስባቸው ጉዳይ በመኖሩ ታውከው እንቅልፍም እንደነሳቸውና መተኛት እንደተቸገሩ ለምእመናን አውጥተው በመናገር እንድጸልዮላቸው ጭምር ጠይቀው ነበር።ደጋግመውም በለቅሶ ስለገለጹት ሁላችንን በሚያሳስብ በመልኩ አዝነን አይዞት ቀስበቀስ ይለመዳል በማለት ለማበረታታት ተሞክሮ ነበር። ውስጠ ምስጢሩን አልተረዳንም። ዳሩ ግን የተቸገሩበት ፣ያስጨነቃቸው ጉዳይ የለመዱትን የአባ ማቲያስን ስም አንስተው ባለመጥራታቸው እንደቀሰፋቸውና መተኛትም እንደነሳቸው ነገሩን በማዋዛት ብቅ ማድረግ ጀመሩ። ከዚህም በመቀጠል ይህን ጉዳይ እየገፉበት በመምጣት በየሳምቱ እሁዱ የእለቱ ትምህርት እየሆነ መጣ።እጅግ ያስጨነቀና ያሳሰባቸው የኅሊ እረፍትም ያሳጣቸው፣እንድንጸልይላቸው ያግባቡን የወያኔውን ፓትርያርክ ስም ሲጠራ እንድንሰማ ነው ። ከዚህ በፊት ያልተደረገና ለሌሎች ያልተፈቀደ ቢሆንም አሁን በእኔ ጊዜ መፈቀድና የፓትርያርኩ የካህት አለቃው ስም ተጠርቶ ካልተቀደሰ እምነታችን እምነት፣ ጸሎታችንም ጸሎት አይሆንም በማለት በቤተ መቅደስ ውስጥ በወንጌል ትምህርት በሚሰጡበት ወቅት ከአንድም ሁለት ጊዜ ስቅቅ ብለው

በማልቀስ የሚያስጨንቃቸውና የሚያሳሳባቸው ይህው ጉዳይ መሆኑን በመሪር ለቅሶ በማንባት ገለጹት። ለብዙዎቻችን አዘን ሆነ። ይህ ነበር የክርስቶስ ተከታዮን ያስለቀሰው?

ቤተክርስቲያናችን ተከፋፍላለች ማለት ችግር እንዳለ በማውሳት የኢትዮጵያ ኦተቤተክ ሥርዓት መከበር አለበት። ቤተክርስቲያናችን ለሦሥት ተከፍላለች ይላሉ እኝህ ቄስ።ነገር ግን ቤተክርቲስያናችን እንኳን ለሦሥት ለሁለትም አልተከፈለች። ቤተክርስቲያናችን አንድ ናት።በነገረ መለኮቱ ላይ ምንም ዓይነት የተለወጠ የለም።ኢትዮጵያም ሆነ በውጭ የኦርቶዶክስ እምነታችን ሳይዛባና ሳይዛነፍ በአንድ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ላይ የተመሰረተና የጸና የኦርቶዶስ እምነት ነው። አው ሥርዓቱ ተበውዟል፣ ፈርሷል። የወያኔ መንግሥት በክርስትና እምነት ላይ ጣልቃ በመግባት ለሱ የሚሰማሙትን፣ በእምነቱና በሥርዓቱ ፅናቱ የሌላቸውን ከአንድም ሁሉት ጊዜ በትእዛዝ አስመርጦ ለባንዳ ሥርዓት የሚያገለግሉ ካህናት ማሰልጠንና ማዋሉ ነው።እዚህ ላይ ነው ሥርዓቱ የተቃወሰው።የዚህን በመፋለሰና የእምነት ተቋሙን ለፖለቲካ መገልገያ የዋለውን ፓትርያርክ አባ ማቲያስን ስም በቅዳሴ ካልጠራሁ ተብሎ ነው የሚለቀሰውና እንቅልፍ የታጣለት።ይህ ደግሞ የተበላሸውን መቀበልና መደገፍ እንጂ በእውነት ለእውነት መቆም አይደለም።

በዚህ ቤተክርስቲያን ከአሁን በፊት የኢትዮጵያውን ፓትርያርክ ስም መጥራት አለብን ተብሎ ከመንፈሳዊ አባቶች ተጠይቆ የምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶና በስፊው ተወያይተንበት በመርሆ አሳቡ ተስማምተን በድምጽ ብልጫ እንደማንቀበልና ሰምም እንዳይጠራ የተወሰነ ጉዳይ ነው። ካህን በተቀየረ ቁጥርም የሚነሳና የሚሻር አይደለም ። በዚህም መሰረት የዚህ ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ሕግና ደንብ፣ የቤተክርስቲያኑ ከፍተኛ ጉዳይ ሁሉ የመላ ምእመናኑን ጠቅላላ ጉባኤ ውይይትና ድምጻቸውንም መሰረት ያደረገ መሆን ሲገባው ይህን በመጣስ የሰበካ ጉባኤው ብቻውን ተሰብስቦ ቄሱ የስብሰባው መሪ በመሆን አራት ለሦሥትና አንዱ ከቦርዱ አባላት እራሱን በማግለል የተካሄደ፣ የመንፈሳዊ ጉዳይ በካህናት ይፈጸም ብለው በሕገ_ወጥ መንገድ ሥርዓት ተካሂዶ በአለፈ ውሳኔ፣ ያለ ጠቅላላው ጉባኤው ስብሰባና ውሳኔ በአንድ ቄስ ፍላጐትና ዓላማ ለማሳከት ከቦርዱ ስውር ደጋፊዎችን በመፍጠ ሊፈጸምና የአባ ማቲያስ ስም ሊጠራ ችሏል። ከዚህም በመቀጠል ሌላው ደግሞ ወደፊት ቀስበቀስ እንደሚቀይሩ ቄሱ ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።እውነት እኝህ ቄስ ለክርስትና ሃይማኖት በሃቅ የቆሙ አባት ናቸው? ለምን ጠቅላላው የምእመናን ጉባኤ እንዲጠራና እንዲወያይ አልውደዱም? ለምን ፈሩ? የሕዝበ ምእመናኑን ውይይት ነፍገውና አፍነው በመስቀል ስም መገዘት ለምን ወደዱ ?ስለፍቅር ማውራት ይህ መሆኑነው?

የዚህ ጉዳይ ክብደትና አካሄድ ያሳሰባቸው ሰዎች ጠቅላላ ስብሰባ እንድጠራ እንዲሁም ቄሱን ለማናገር ብዙ የተደጋገሙ ሙከራዎች ቢደረጉም ሁሉም ጆሮ ዳባ ልበስ ሆነና መልስ የሚሰጥ ጠፍቶ በአቋራጭ የሚፈልጉትን ለማሟላት ሕግ ጥሰቱንና አምባገነናዊ የስውር አካሄዱ እየጐላ መጣ።ቄሱ ቤታቸውን ትተው በመውጣት እንቅልፍ መተኛት ስለአልቻኩ በዘመድ ቤት ነው ያለሁት እያሉ በመሰወር ተዶለተ። ሰው በጉዳዮ እንዳያናግራቸው ማሶገጃ የፈጠሩት ዘዴ እንጂ የከፋ የጎሊና በሽታ ራስን ለማጥፋት ያቀረበ የሰው ጠባቂ አስፈልጐ ከቤት የሚያሶጣ አይደለም።ከሆነም ሃኪም ቤት ነው መሄድ የሚያስፈልገው።ይህ የስውር አጀንዳ ሴራና ወያኔዊ ስውር በክፋት የታጀበ አካሄድ ነበር።የሕዝብ ሙብትና ስሜት መናቅና መርገጥ ክርስቶሳዊ መንገድም እምነትም አይደለም።ክርስቶስ ያመናችሁ ተከተሉኝ አለ እንጂ አላስገደደም። አባታችን ለምን በእምነት ፈንታ ለሥርዓት አጎልብተው እንደያዙ፣ ተገዥና ተንበርክኮ አማኝ እንዲንሆን መረጡ ? ለምንስ ከሕዝበ ምእመናን ርቀው ከሥርዓት ውጭ የሲኖዶስ ሕግና ውሳኔዎችን ደጋግሞ

ላፈረሱና ላልተቀበሉ ፓትርያርክን ለማስቀደም ወደዱ? ያስለቀሰውና እንቅልፍ ያሳጣው በእውነት በኢየሱስ መንገድ አለመሄድ ከማዘን ውይንስ የሥርዓት የአባ ማቲያስ ስም አለመጠራት?

ለእውነት መቆምና ስለእውነት አለቅሶ መከራከር እግዚአብሔር የሚወደውና የሚፈልገው መልካም ምግባር ሆኖ ሳላ አንዳንድ አባቶች የውንጌል መልዕክቶችን በመጥቀስ የአነጋገር ዘይቤ በማሳመርና በጥሩ ቃላት ማዥጎድጎድ በአፋቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ያላቸው ከልባቸው ግን የራቀ ሞልተዋል።በጣሊያን ወረራ ጊዜ ብዙ ጳጳጾች ለባንዳ አድረው ገዝተዋል ሕዝብ አስጨርሰዋል። አይገርመንም። እኚህ ቄስ ሲያስተምሩ በእውነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ፈቃድና ለእውነት ያደሩ፣ የሚሰብኩት የወንጌል ቃልና መልዕክት የሰውን ስሜት በተመስጦ የሚጋብዝና የሚያሳምን ይመስላል። ጥሩ አባት አገኘን ብለን አጀማመራቸው መልካም ነው በማለት ተስፋ አድርገንም ነበር። ይሁን እንጂ፣ ለእውነት ክርስትና እምነት ፍቅር ወደ እግዚአብሄር ዘወር ብለው በማልቀስ ፈንታ ወደ ሰው ዞረው በማልቀስ ሰውን በማሳመን ፣ ፍቅሩ የአባ ማቲያስና የሥርዓት ሆኖ ጥረታቸው ለምድሩ ዓለም ለመሆኑ በግልጽ ታየ።

ቄስ፣ መጋቢ አዲስ ይልማ ቸርነት በነአባ ገብረመድን ተምረው በነ አባ ማቲያስ በሹመት የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዲሬክተር ማዕረግ አስተዳደር የደረሱበት የሚያውቁትና የተቀበሉት እውነትነትና ትክክልም ነው ብለው አምነው ሲመሩበትና ሲሰሩበት የቆዮት በወያኔ አስተዳደር ጣልቃ ገብነት ከኦርቶዶስ ተዋሂዶ ሲኖዶስ ሥርዓት ውጭ የተፈጸመ የፓትርያክ እጩነትና አሰገድዶ ማስመረጥ ለማንም ግልጽ ነው።ለዚህም አይነት ያደሩ በመሆን እውነቱ በትክክል አልታያቸውም። የክርስትና ሃይማኖት አባቶች ለእውነት የተናገሩ፣ በሃቅ የቆሙ የካህናት በደል፣ መገደል፣ ቤተክርስቲያን እንዳትደርስ የተከለከሉ፣ቤተክርስቲያን መፍረስና መቃጠ፣ገዳማት ሲፈርሱና ሲታረሱ፣ ያለበደላቸው ቅጠል በልተው አፈር ልሰው ለአገርና ለሕዝብ ቀን ከሌሊት የሚጸልዮ አባቶች መባረር፣ መታሰርና መንገላታት፣ መገደል፣በውሸት የመነኲሴ ልብስ በለበሱ ሲሰለሉ፣ሲኖዶስ ከአንድም ሁለት ጊዜ ያሳለፈው ውሳኔ ሳይፈጸም መቅረት፣ የእምነትና የሥርዓት መዛባትና መበላሸት፣የሕዝብ በደል፣ስቃይና ወህኒ ቤት ሲወረወሩ፣ሕዝብ በገዛ አገሩ ሲፈናቀል፣ ሲሰደድ፣በግፍ ሲሰቃይና ሲዋረድ፣አገር ሲሸጥና ድንበር አሳልፎ ሲሰጥ ይህን መሰል ሁሉ ስቃይ ዓይተውና ሰምተው እርቅ(ምህላ) የማይጠይቁ እንዳውም ዋናው የወያኔ እጅ ሆኖ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን በቅዳሴ መጥራት ለምን አስፈለገ? ለዚህ ሁሉ በደል መረጃ ባለበት በ21ኛ ክፍለ ዘመን በዚህ የወንጀለኛ ሥርዓት እያገለገለች ያለች ቤተክርስቲያን ሥር ለማስገባት ማቀድ ሕዝበ ክርስቲያኑ አያውቅም ብሎ በነፃነት በምንኖርበት አገር በሃይማኖት ስም ፍቅር ጠፋ ብሎ ማንባትና እጅ ለመጠምዘዝ መሞከር እንደመናቅና መዘለፍ ይቆጠራል።

ስለዚህ እኚህ ቄስ የቆሙለትን ዓላማ በሚገባ የሚያውቁትና የኖሩበት፣ የተቀበሉትና አገልግሎትም የሰጡበት በመሆኑ ይህን ለማሳካት፣ አባ ሚቲያስ በወያኔ ፍላጎትና እጩነት በካህናት ላይ ተጽኖ በማድረግ የተካሄ ምርጫና  የተመረጡ ፓትርያርክን  ስም ጠርቸ ካልቀደስኩ እምነቴ ይነካል፣ሥርዓት ይፋለሳል ብሎ ማልቀስና ምእመናንን መገዘት ከእውነት የራቀ የሥርዓት እምነት እንጂ ክርስቶሳዊ አይደለም። በክርስትና እምነት ስም አገልግሎቱ ለወያኔ አምባገነን ሥርዓት የሚጠቅም፣ የክርስትና ሃማኖታችንን ፣ አገርና ወገንም የሚያሳዝንና የሚጐዳ በመሆኑ የኚህ ቄስና ተባባሪዎች ድርጊትና አካሄድ በአስቸኳይ እንድቆም እየጠየቅን ትግላችን ይቀጥላል ቤተክርስቲያናችን ከባንዳዎች ይጸዳል።

## እውነት በሌለበት ሰላም ፍቅር የለም ! የእውነት አምላክ ፍትህን ያቅርብልን!